

# ጳውሎስ በአቴንስ

- ጳውሎስ ሲላስንና ጢሞቲዎስን በአቴንስ እየጠበቃቸው በከተማይቱ ጎዳናዎች እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ብዙ የሚያማምሩ ሕንፃዎችን ተመለከተ። በተጨማሪም በርካታ ጣኦታትን ተመለከተ። ሰዎች ድንጋይ ወይንም እንጨት ከጠረቡ በኋላ ምስሎችን ይሰሩና አማልክቶቻችን ናችሁ እያሉ ይጠሯቸው ነበር። ልክ ኃይልና ስልጣን ያላቸው ይመስልም ለእነኝህ ምስሎች በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዱላቸውና ያመልኳቸው ነበር።

- ደግሞም ምስል ያልተቀረፀለት ምንም አምላክ እንደሌለ እርግጠኛ ለመሆን በማሰብ አንድ ምስል ሰርተው፣ “ለማይታወቅ አምላክ” የሚል ፅሑፍ በምስሉ ላይ ፅፈውበት ነበር። ጳውሎስም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም፣ “እኔ ስለዚህ አምላክ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፣” አላቸው። ከዚያም ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በምድር ውስጥ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ስለፈጠረው እውነተኛው አምላክ ነገራቸው። ከዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር ስለመምጣቱ፣ ስለመገደሉና ከሞትም ስለመነሳቱ ጨምሮ ነገራቸው።

- የአቴንስ ሰዎች ከሚገባው በላይ ጉጉታቸው ጨመረ። አዳዲስ አሳቦችን መስማት ይሹ ነበር። ይህ ጳውሎስ የሚናገረው ንግግር ደግሞ አዲስ አሳብ ነው። አንዳንድ ሰዎች የጳውሎስን ስብከት ሰምተው በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ።

- አቴንስን የመጎብኘት እድል ቢያጋጥማችሁ ትልቅ የሚባለው ኮረብታ ላይ ወጥታችሁ አክሮፖሊስን ማየት ትችላላችሁ። ጳውሎስ ለአቴንስ ሰዎች በሰበከበት ወቅት የጎበኛቸውን ሕንፃዎችም ማየት ትችላላችሁ። ጳውሎስ በነበረበት ጊዜ የሕንፃዎቹ እድሜ 400 ዓመታት ያህል ነበር። እነኛ ሕንፃዎች ዛሬ ዕድሜያቸው ከ2400 ዓመታት ይበልጣል።

*ይህ ጳውሎስ በአቴና ያደረገውን ቆይታ ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17፡ 16 – 33 ውስጥ እናገኘዋለን።*

http://gardenofpraise.com